# ከመድረክ የአሜሪካ ጉብኝት ምን ይጠበቃል?

መክብብ ማሞ mekbma@yahoo.com

የስምንት ፓርቲዎች ጥምረት የሆነው መድረክ ከፍተኛ አመራሮች በአሜሪካ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ እንዲሁም በመጪው ምርጫ ዙሪያ በውጪ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ድጋፍ ለማግኘትና ያለውንም ለማጠናከር ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ወደ አሜሪካ እየገቡ ይገኛል:: አቶ ገብሩ አስራት ፣ ኢንጂኔር ግዛቸው ሽፈራው እና ዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳ የሚገኙበት ቡድን ያለፈው ቅዳሜ በሲያትል እንዲሁም እሁድ በሳን ሆዜ ከተሞች ስብሰባዎችን አድርገዋል:: በመቀጠልም በመጪዎቹ ቀናት በላስ ቬጋስ ፣ በአትላንታ እንዲሁም በዋሽንግተን ዲሲ ቆይታ በማድረግ ስብሰባዎችን ለማካሄድ ማቀዳቸው የወጣው መርሃ ግብር ያስረዳል:: በአቶ ስየ አብርሃ የሚመራው ደግሞ ዳላስንና ሌሎች ከተሞችን እንደሚያዳርስ ተዘግቧል::

በእኔ ግምት በአሁኑ ጊዜ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ከመቼውም ጊዜ ባነሰ መልኩ በአገሩ ላይ ስለሚካሄደው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስሜት ያጣበት ወቅት ይመስለኛል:: በተለይ ባለፈው ምርጫ የቅንጅት አመራሮች ከእስር ከወጡ በኋላ በመካከላቸው የተከሰተው መከፋፈል ያስከተለው ልዩነት አሁንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲንጸባረቅ ይታያል:: የቅንጅት ምርጫውን ማሸነፍ የፈነጠቀው ተስፋ እንዲሁም አመራሩ ወደእስር ቤት ሲገባ የነበረው ሁኔታ በውጪ ላለው ኢትዮጵያዊ በአንድነት መሥራት እና መተባበር ጉልህ ድርሻ የነበራቸው እውነታዎች ነበሩ:: ይህም አመራሮቹ ከእስር በኋላ በተለያዩ የአውሮፓ ፣ የአሜሪካና አፍሪካ አገራት ባደረጉት ጉብኝት ከህዝቡ ያገኙት ድጋፍ በራሱ በማስረጃነት የሚጠቀስ ነው::

ከዚህ በኋላ ግን በአመራሮቹ መካከል የተከሰተው መከፋፈል በተለይ በውጪ ያለውን ደጋፊ ጎራ እየለየ ሲያናቁርና ሲያጋጭ የቆየ ርዕስ መሆኑ እስካሁን ድረስ የሚታይ ነው:: የዚህ ቁርቋሶ ውጤትም የቅንጅት ወራሽ ነኝ የሚለው አንድነት ፓርቲ የተቋረጠውን ትግል ለመቀጠል እና እንደ ፓርቲ ለመደራጀት ከዓመት በላይ ጊዜ እንዲወስድ ካደረጉ ምክንያቶች በዋንኛነት የሚጠቀስ ነው:: ከዚህም በኋላ የቅንጅት ትኩሳት ሲበርድ አብረው «ወራጅ አለ» በማለት ከተሳትፎ የወረዱትን ጭራሹንም ከፖለቲካው እንቅስቃሴ ፍጹም የራቁትን ቤት ይቁጠራቸው:: ጉዞአችንን የቀጠልነውና እስካሁንም ባገኘነው አጋጣሚ እንዲሁም በትርፍ ጊዜያችን በፖለቲካው ዙሪያ ብቅ ጥልቅ የምንለው ግን በአገር ቤት መካሄድ ስላለበት የትግል ስልት ፣ ስለሰላማዊና ሰላማዊ ስላልሆነ ትግል ልዩነት እና ተመሳሳይነት ፣ ስለ ትጥቅ ትግል ብቸኛ አማራጭነት ፣ ሰላማዊ ትግልን በትጥቅ ትግል ስለመደገፍ ፣ ስለመድረክ ህጋዊነት ፣ የአንድነት ፓርቲን ስለተቀላቀሉት ግለሰቦች የመደብ ጀርባ ፣ ስለ ስየ ይቅርታ መጠየቅ ወዘተ እየተነታረክን እንገኛለን:: በዚህ ሁሉ መሃል ግን በውጪ ያለውን ኢትዮጵያዊ በአንድነት አያይዞት የሚገኘው ቀጭን ገመድ የብርቱካን እስርቤት መግባት ነው:: ስለብርቱካን መፈታት ቀን ተሌት ከሚተጋው ኢትዮጵያዊ ውስጥ የአንድነትን ፓርቲ የማይደግፈው እንዲሁም የመድረክን ሕጋዊነት የማይቀበለው ቁጥር ስታቲስቲካዊ መረጃ ባይኖረኝም ትንሽ ነው የሚባል አይደለም:: ከብርቱካን መፈታት በኋላ ይህ ሕብረት የእንባይ ካብ እንደሚሆን አሁን ያለው መሠረት የማያሻማ ማስረጃ ይሰጣል::

ይህን ሁሉ ያነሳሁት የመድረክ አመራሮች በዚህ ጉብኝታቸው የሚጠብቃቸው ፈተና ቀላል እንደማይሆን መሠረት ለማስያዝ ነው:: በስብሰባቸው ላይ በመገኘት የሚሳተፈው ሕዝብም አንድነትንም ሆነ መድረክን እንደ ፓርቲ መደገፍ ቢፈልግም በተለይ መድረኩ በመጪው «ምርጫ» የመሳተፉ ጉዳይ ሌላውና ምላሽ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው:: በመሠረቱ የአንድነት መሪ እስርቤት ሆና «በምርጫው» ለመወዳደር መወሰን አሸንፎ ሥልጣን ከመያዝ አኳያ ፋይዳ ያለው ነው ባይባልም ፓርቲው ግን በኢትዮጵያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለዚህ ውሳኔ መድረሱ በአክብሮት የሚታይ ነው::ሆኖም ግን ይህን በምርጫ የመወዳደር ውሳኔ በውጪ ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ አቅርቦ ማሳመን የመድረክ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

አመራሮች አንዱ ተግባር ሲሆን ሌላውና ምናልባትም ዋንኛ ሊሆን የሚገባው ሥራቸው ደግሞ ከምርጫው በኋላ ምን ሊያደርጉ እንዳሰቡ ለሕዝቡ ማስረዳት ይመስለኛል፡፡

ለዚህም ነው ሲያትል በተደረገው ስብሰባ ላይ ጠያቂዋ ሴት ከምርጫ በኋላ ሊፈጽሙት ስላሰቡት ተግባር ሽሙጥ አዘል ጥያቄ ያቀረበችው፡፡ የግለሰቧ ጥያቄ አግባብነት ያለው ብቻ ሳይሆን በውጪ ያለው የብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ጥያቄ ነው ለማለት በአሃዝ የተደገፈ ማስረጃ ማቅረብ የሚያሻው አይመስለኝም፡፡ በመድረክ ሥር የተሰባሰቡት ፓርቲዎች አብላጫውን የኢትዮጵያን ድምፅ አግኝተው እንደሚያሸንፉ በቅንጅት ጊዜ የተከሰተው በቂ ማስረጃችን ነው፡፡ ጥያቄው ግን «ካሸነፉስ በኋላ?» የሚለው ነው፡፡ በመሠረቱ በኢንጂኔር ግዛቸውም ሆነ በዶ/ር ነጋሦ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ነው ለማለት አልችልም፡፡ ኢ/ር ግዛቸው ሲመልሱ «ገዢው ፓርቲ 3000 ወጣቶችን በገንዘብ በመግዛት ድምፅ ማግኘት ይችል ይሆናል ግን የ14 ሚሊዮን ሥራ አጥ ወጣቶችን ድምፅ መግዛት ይችላል ወይ?» ነበር ያሉት፡፡ የእኔ ጥያቄ ግን «ባይገዛስ?» የሚለው ይሆናል፡፡ ኢ/ሩ እንዳሉት ሥራ አጦች በአገራቸው ለውጥ እንዲመጣ ይፈልጋሉ ስለዚህ የለውጥ አራማጅ የሆነውን ፓርቲ ይመርጣሉ፡፡ በዚህ ላይ ቅንጣት ልዩነት የለንም ሆኖም ግን ዋናው ጥያቄ «ከምርጫውስ በኋላ ጥያቄያቸው ተግባራዊ ይሆናል ወይ?» የሚለው ነው፡፡ ዶ/ር ነጋሦ ተቀብለውም «የግንቦቱን ምርጫ እንደምናሸንፍ እርግጠኛ እንድንሆን ያደረገን የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ወጣቱ በአገሪቷ ላይ የዴሞክራሲ አስተዳደር እንዲሰፍንና የፍርሃት ዘመን እንዲያበቃ ቁርጠኛ መሆኑን በመመልከታችን ነው» ብለዋል፡፡ ይህ አመለካከት በውጪ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ያላንዳች ተቃውሞ ሊጋራው የሚችል ሃሳብ ነው፡፡ ጥያቄው ግን «ከምርጫ ድል በኋላ የምርጫው ተስፋ እንዴት ነው ተግባራዊ የሚሆነው?» የሚለው ነው፡፡

«አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊያን» ብለው የሰየሙት ወያኔዎች ከወራቶች በፊት ተሰብስበው ኢትዮጵያን ለሚቀጥሉት 5 ዓመታት እንዴት እንደሚመሩ ዕቅድ ነድፈው ውሳኔ አስተላልፈው ጨርሰዋል፡፡ «ካለፈው ምርጫ ብዙ ተምረናል» እያሉ የሚለፍፉት ወያኔዎች ግንቦት ላይ ለመድረክ ሥልጣን እንካችሁ ብለው የምኒልክን ቤተመንግሥት ለቀው ወደ ሰላማዊ ሥራ ይሰማራሉ ብሎ የሚያስብ ካለ ጤነኛ ለመሆኑ የሃኪም ማረጋገጫ ቢጠየቅ የሚከፋው አይመስለኝም፡፡ ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ በውጪ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ ድጋፍ ለማሰባሰብ ጥረት ላይ የሚገኙት የመድረክ አመራሮች የብዙሃኑን ድጋፍ እንዲገኙ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አጥጋቢ መልስ መስጠት ያሻቸዋል፡፡ የብዙዎቻችንም ጥያቄ በእነርሱ ማሸነፍ ላይ ሳይሆን ከምርጫው በኋላ ሊያደርጉት ስላሰቡት ዕቅድ ነው፡፡

ልክ እንደባለፈው ሁሉ በአስተያየትና በኮታ የሚሰጣቸውን «የፓርላማ መቀመጫ» ተቀብለው «ትግላቸውን» ይቀጥላሉ? ወይስ ሕዝቡን ለክፍል ሁለት ትግል ያዘጋጁታል? «ሰላማዊውንና ሕጋዊውን ትግል» ከምርጫው ማግስት እንዴት ነው የሚቀጥሉት? እንደተለመደው የመታሰር ዕጣ ሊያጋጥማቸው ይችላል ፣ በዚያን ጊዜ ትግሉን እንዴት ነው ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርጉት? መራጩ እነርሱን በመምረጡ ከ1997ቱ ምርጫ በከፋ መልኩ ግድያ ፣ እስራትና እንግልት እንደሚደርስበት እያወቀ የሚሰጣቸውን ድምፅ እንዴት ነው ወደተግባር የሚቀይሩት? ከምርጫውስ በኋላ እንዴት ነው የመራጩን ሕዝብ ድምፅ የሚጠብቁት? ባጠቃላይ ከምርጫ በኋላ ሊያደርጉ ያሰቡት ዕቅድ ምን ይመስላል የሚል ነው፡፡ ይህንን ስንጠይቅ ግን ያላቸውን ዕቅድ በሙሉ ዘርግፈው ወያኔ እንዲሰማ ያድርጉ ማለታችን እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ባጭሩ እነዚህንና የመሳሰሉ ጥያቄዎች በውጪ የሚኖር የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን በማጤን የመድረክ አመራሮች ስብሰባ በሚያደርጋቸው ከተሞች አቅጣጫ ጠቋሚ ምላሽ ለመስጠት ቢዘጋጁ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ድጋፍ ከማስገኘቱ ባሻገር ጉዞዋቸው ስኬታማ እንዲሆን ያደርገዋል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ አለበለዚያ ግን ጉብኝታቸው ለመገናኛ ብዙሃን ፍጆታ ብቻ የሚውል ተራ ዜና ይሆናል፡፡

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com